# በሟች በድን ገዙን!

ከዓሣዬ

ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ
የተሰኘው ይትባሕል ቢያሣዝንም ቅሉ
ቀኑ ተለዋውጠ ጉዱ ተገላብጠ
በ ኣራቱም ማዕዘን ዜጋ ተጠራርቶ
የጥቁር ጀግና ሃይል ነጩን ኣሯሩጠ
እንዳላባረረው ከኣገሩ ጠራርጎ ፡
ቀኑ ጎደለና ብርሃን ጨልሞብን
በባንዶች መገዛት ውርደት ሣያንሥብን
ግዜው ጣለንና በሟች በድን ገዙን ?

ሁሌ እየዘመሩ የመለስ እራዕዩን
የእሬሣውን ትንፋግ ፀበል እየረጩን
የባንዳን ከርሥ ኣደር ቅርሻት እየጋቱን
በዘር ፖለቲካ ከረድፋቸው ገብተን
ከድጥ ወደ ማጡ ከጎጣቸው ወርደን
ማቀርሸት ያዝን እኮ እንደ እነሱ ጠበን ! ።
ጎበዝ እኮ ታድያ !
መፍትሄው ይሄው ነው ? እሥቲ መላ ምቱ !
የዘረኛን ቅርሻት እንዳለ እየጋቱ
ልክ እንደ ዘረኛው ወርዶ እየዘቀጡ
በቀደዱልን ቦይ ይሻላል መፍሰሱ ?
ወይሥ ?
የመጥረቢያ እጀታ ሆኖ ከማጎብደድ
በኢትዮጵያነት ጸንቶ ዘረኛን በማንጎድ
ከርሥ ኣደር ሹምባሹን ታግለን በማሥወገድ
እንደ ኣንድ ዜጋ መቆም ! በዘር ሣንታገድ ?

እንደ እኔ ከሆነ በድን አይገዛንም
በባንዳ ቦይ መፍሰሥ ከቶ ኣያምርብንም
ለኣገር ሕልውና በጋራ ተነሥተን
ዘረኛ ወያኔን በሕዝብ ሃይል ኣዳሽቀን
የዜግነት ግዳጅ ቃል ኪዳን ኣንግበን
በሟች ሥንገዛ ታሪክ እንዳይከሰን
ኢትዮጵያን ከውድቀት እናድን ተባብረን ! ።

*11/01/2014 GC*